# መጥፎ ስሜት ከተሰማዎት

ስለምልክቶችዎ ከሓኪምዎ ጋር ይነጋገሩ

## 1 እርምጃ የቤተሰብ ሓኪምዎ ጋር መሄድ




### የቤተሰብ ሓኪሞች ምርመራዎችዎንና ሪፈራሎችዎን ያቀናጃሉ

የቤተሰብ ሓኪሞች በሚከተሉት ነገሮች ላይ ትልቅ ሚና ይጫወታሉ።

- ምልክቶችዎን መረዳት
- ምርመራዎችን ማዘዝ(እንደ የሽንት፣ የደም፣ ወይም የራጂ)
- ከሌሎች የጤና ኣገልግሎቶች እና ልዩ ባለሞያዎች ጋር ማገናኘት (ለምሳሌ፥ ለባዮፕሲ ወይም ለቀዶጥገና)

## 2 እርምጃ ምርመራ



### ምርመራዎቹን ለማድረግ ወደተለያዩ ቦታዎች መሄድ ሊኖርብዎት ይችላል።

- በቀጠሮዎ ለመገኘት እርዳታ የሚያስፈልግዎ ከሆነ ለሓኪምዎ ይንገሩ።
- የምርመራ ቀጠሮ ለማስያዝ ጊዜ ኣይውሰዱ።
- በተቻለ ፍጥነት ምርመራዎችዎን ለማድረግ ይሞክሩ

እባክዎን " ለሓኪምዎ የሚጠይቁት ጥያቄዎች" የሚለውን ክፍል ይመልከቱ።

## 3 እርምጃ ሕመምዎን ማወቅ




### ሁሉም ምርመራዎች የቤተሰብ ሓኪምዎ ችግር ካለ መረዳት እንዲችሉ ይረዳሉ።

ሓኪምዎ፥

- የምርመራ ውጤትዎን ያስረዳዎታል
- ማንኛውም ህክምናዎችን ወይም እንክብካቤዎችን ያቀናጃል
- ኣስፈላጊ ከሆነ ከልዩ ባለሞያዎች ጋር ያገናኝዎታል።

CC BY NC ND

ከህዳር 5፣ May, 2025
ጽሑፍ፥ አልበርታ የካንሰር እንክብካቤ፡ አልበርታ የጤና አገልግሎ

Alberta Health Services

Physician Learning Program

# ስለምርመራዎችዎ ለሓኪምዎ የሚተይቁት ጥያቄዎች

- ምርመራው ምን ምን ያጠቃልላል?
- ምን ዓይነት ምርመራዎች ጥቅም ላይ ይውላሉ?
- ለምርመራው የሚያስፈልጉ ዝግጅቶችና ቀጠሮ ማስያዝ ማን ያደርገዋል?
- ምርመራው የሚካሄደው የት ነው?
- ለምርመራው የሚያስፈልጉ ቅድመ ዝግጅቶች አሉ?
- በምርመራ ወቅት ከእኔ ጋር ሌላ ሰው መሄድ አለበት?
- ምርመራው ምን ያህል ጊዜ ይወስዳል?
- የምርመራ ውጤቱን ማንነው የሚያስረዳኝ?
- የምርመራ ውጤቱን ግልባጭ መውሰድ እችላለሁ?
- ውጤቱ ጥሩ ካልሆነ ምን ይከሰታል?
- ሌላ ምን ዓይነት ምርመራዎች መደረግ አለባቸው? ለምን?

?



811 Health Link
Advice 24/7

**ሐኪም ለማግኘት እርዳታ ሲፈልጉ 811 ይደውሉ**
**https://albertafindadoctor.ca/**
የትርጉም አገልግሎት ሊኖር ይችላል

Alberta Health Services | Physician Learning Program

CC BY NC ND
ከህዳር 5፣ May, 2025
ጽሑፍ፥ አልበርታ የካንሰር እንክብካቤ፡ አልበርታ የጤና አገልግሎ